# በመመዘኛዋ ኤርትራ ጦስ-ዛሬም ስንተራመስ

ይሄይስ ተአምኖ/ጀርመን

*- ለኤርትራ ነፃነት ሙሉ ዋስትና ለመስጠትና ይህንንም ነፃነት በተደላደለ መሠረት ላይ ለማቆም የሚቻልበትን መንገድ ለመቀየስ፣ የተካሄደ ጉባዔ፣*

*- ለመሆኑ ኤርትራዉያን በእኛ በኢትዮጵያዉያን ስብሰባ ላይ እንዲገኙ፣ በሬ ቀርቶ፣  ዶሮ ማረድስ ያስፈልግ ነበር ወይ?*

*- „..ኢትዮጵያና ኤርትራ - ዛሬም ያልተጠናቀቀ ፍቺ፣ ያልተሳካም  ጉርብትና... „*

*- „... የኤርትራ ነገር፤ የኛ ችግር፤ መርህ አልባ ፍቅር...„*

በምናብ-ዓለም ደረጃ የወደፊቷ ኢትዮጵያ ዕጣ-ፋንታ መወሰኛ መዲና እየመሰለች በመጣችዉ የዋሽንግተን ከተማ የኢትዮጵያንና የኤርትራን-የትናንት፣ የዛሬንና የነገን ግንኙነት አስመልክቶ በቅርቡ አንድ ዓቢይ ጉባዔ መካሄዱ ይታወሳል። የመድረኩ አዘጋጆችም ኢሳትና ቪዥን ኢትዮጵያ የተሰኙ ተቋማት እንደሆኑ ለጉባዔዉ ታዳሚዎች በይፋ ተበሥሯል። ጉባዔዉ መካሄዱ ባልከፋ ነበር። ግን በጉባዔዉ ላይ የታዩት ክስተቶች የኢትዮጵያውያንን አንጀት የሚያቃጥሉ እንጅ አንጀት አርስ ሁነዉ አልተገኙም። በዚህ አባባሌ የሚከፋም፣ የሚደስትም ወገን እንደሚኖር አልጠራጠርም። አነሳሴ ማናቸዉንም ወገን ለማስከፋትም ሆነ ለማስደሰት እንዳልሆነ ግን፣ አንባቢ እንዲረዳልኝ እሻለሁ። በእኔ እምነት አንድ ሰዉ በሀገሩ ጉዳይና በሚከተለዉ እምነት አንደኛዉን ወገን የማስደሰትም ሆነ፣ የማሳዘን ይሉኝታ እጅ ከወርች ሳያስረዉ በአደባባይ አቋሙን መግለፅ መቻል ይኖርበታል። እንደ አንድ ዉሎ ገብ ኢትዮጵያዊ ዜጋም በጉባዔዉ ላይ የተነሱት ርዕሰ-ጉዳዮች የሁለቱን ሀገሮች የወደፊት ግንኙነት አስመልክቶ የተንሸዋረረ አቋም በመንፀባረቃቸዉና በአጠቃላይም አካሄዳቸዉ በተለይ ሀገራችንን ኢትዮጵያ የሚጎዳ መስሎ ስለታየኝ፣ ብቻን ከመናደድ አብረን እንድንቃጠል ወይም የጋራ መፍትሄ እንድንሻ ነዉ። መቼም አንድ ሀገር ለድርጅቶችና ለምሁራን ብቻ በግል የተበረከተች ስጦታ እንዳልሆነች ሁላችንም የምንተማመን ይመስለኛል። ኢትዮጵያ የነጂድ ካሳ ከበደ፣ የነዶ/ር ጌታቸዉ፣ የነበረከት ስምኦን ወይም የነስብሃት ነጋ የግል ሀብት አይደለችም። ስብሰባዉ በአብዛኛው በድርጅታዊ ሥራ የተመረጡና ለተወሰነ ዓላማ ብቻ በቆሙ ስብሶቦች የተሞላና ለኤርትራ በአጋፋሪነት እንዲያገለግሉ የተሰለፉበት ቢሆንም እንደዚያች ሀገር ዜጋ  ሁላችንንም ያገባናል፣ የሁላችንም ነች፣ አራት ነጥብ። በዚህ ስብሰባ ላይ እንደነ ካሳ ከበደ ዓይነቱ ተጋብዞ „.. መቼም ፕሬዚዴንት ኢሳይያስ ስለኢትዮጵያ መበታተን ያስባሉ የሚባለዉን ነገር እኔ በምንም ዓይነት መንገድ የማምንበት (የምቀበለዉ) ጉዳይ አይደለም...„ የሚለዉን ዓይነት ቅጥፈት የተሞላበት ምሥክርነት ከሚያሰሙን፣ የጎጃሙን ገበሬ የየትኖራ አምራቾች ማኅበር ሊቀ መንበር የነበረዉን እንዳይላሉ መኮንን ወይም የብቸናዉን ተሾመ ዘለቀን ጋብዛቹሃቸዉ ቢሆን ኖሮ፣ ዕዉነቱን ይነግሩን ነበር። የእነሱ ተፈጥሮ ዕዉነቱን ተናግሮ ከመሸበት ማደር ነዉና። የዋሽንግተኖቹ መዋያቸዉ እንጅ ማደሪያቸዉ አይታውቅም። ብዙዎቹ ኒቆዲሞሳዉያን ናቸዉና።

ይህ የአሁኑ ጉባዔ ከመካሄዱ በፊት፤ ሁለት የኢሳት ጋዜጠኞች (ፋሲል የኔዓለምና መሳይ መኮንን ይመስሉኛል) በአንድ ወቅት ኤርትራ ደርሰዉ እንደተመለሱ፣ ስለተልዕኳቸዉ ገለፃ ለማድረግ እንዲሁ አንድ ስብሰባ ዋሽንግተን ላይ ተካሂዶ ነበር። በስብሰባዉም ላይ ኤርትራዉያን ወንድሞቻችንና

እህቶቻችን ተሳትፈዋል። የመጀመሪያዉ ችግር የተንፀባረቀዉም በዚህ ስበሰባ ላይ ነበር። የስብሰባዉ ዓላማ ባጭሩ በኤርትራ በኩል የትጥቅ ትግል እናራምዳለን ስለሚሉት ተቃዋሚ ኀይሎች በእውን ስለመኖራቸዉ በመሬት ላይ ያለዉን ዕዉነታ የአካል ምስክርነት ለመስጠትና ደጋፊዎቻቸዉም የእርዳታ እጃቸዉን የሚዘረጉበትን መንገድ ለመሻት ነዉ (ምንም እንኳዋ ከጋዜጠኝነት ሙያቸዉ ይልቅ የድርጅት ካድሬነታቸዉ አሸንፏቸዉ ቢታይምና ጎልቶ ቢወጣም፣ የኤርትራዉን የደህነት ሰዉ እንደ እየሱስ ክርስቶስ አድርጎ ሥሎ ማቅረብና የሓዋርያቱን የኢሳትን ጋዜጠኞች እግራችንን አጠበን ዓይነቱ አቀራረብ ሳንረሳ ማለቴ ነዉ)። እግረ-መንገዳቸዉንም ፕሬዚዴንት ኢሳይያስን ቃለ መጠይቅ በማድረግ የኢትዮጵያንና የኤርትራን ግንኙነት አስመልክቶ፣ እንደ እምነታቸዉ መልዕክት እንዲያስተላልፉ አድርገዋል። በዚህም ምክንያት ይመስላል በዚህ ስብሰባ ላይ ቁጥራቸዉ ቀላል የማይባል ኤርትራዉያን ተገኝተዉ ነበር። መገኘት ብቻ አይደለም፣ ተዘባብተዉብናልም። ወደ ሌላዉ ዝባዝንኬ ሁሉ ሳልገባ አንድ የስብሰባዉ ታዳሚ የሆነ፣ ኤርትራዊ የተናገረዉን ብቻ መጥቀሱ የሚበቃ ይመስለኛል። የተናገረዉን ቃል በቃል ሳስቀምጠው „... ከዛሬ ሦሥት ወር በፊት በሬ አርዳችሁ አንኳን ብትጠሩን አንመጣም ነበር...„ ነዉ ያለዉ። እዚህ ላይ ነዉ ጥያቄዉ፤ ለመሆኑ ኤርትራዉያን እኛ ስብሰባ ላይ እንዲመጡ ምን ስለሆኑ ነዉ በሬ ቀርቶ ዶሮስ ማረድ የሚያስፈልገዉ? ተሳታፊዎቹ የዉስጥ መመሪያ እንደተሰጣቸዉ የሚያስታዉቀዉ ለዚህ ኤርትራዊ አባባል አንድም ትንፍሽ ያለ ኢትዮጵያዊ አልነበረም። ወዮላችሁ ኢሳይያስና ሻዕቢያን የሚያስቀይም ነገር ብታነሱ፣ ዓይነት ቀጭን መመሪያ ዉስጥ ለዉስጥ የተላለፈች በሚመስል መልክ ነዉ ስብሰባዉ ተደምሞ ያለፈዉ። በመሠረቱ የሁለቱ ሀገሮች የወደፊት ግንኙነት ዕጣ-ፋንታ የሚወሰነዉ በጉቦና ፍሪዳ በመጣል አይደለም። ወይንም ደግሞ የተወሰነን ክፍል ሥልጣን ላይ ለማምጣትና ለኢትዮጵያ ሠይጣን የሆነዉን ሻዕቢያን መላክ ነዉ ብሎ በማቅረብ አይደለም። ትክክለኛ በሆነ የሀገሮች የግንኙነት መርህ ላይ በተመሰረተ ፖሊሲ በመቅረፅ ነዉ። ይህን እስካላደረግን ድረስ መቶ ጊዜ ጉባዔዎች ቢካሄዱ፣ ምሁራንም ፅሁፎቻቸዉን ቢያቀርቡ፣ ኢሳይያስንም ብናወድስና ግርማ ሞገሳቸዉንም ከፍ ከፍ ብናደርግ በመሬት ላይ አግጠዉ ኪሚታዩት ችግሮቻችን ፈቀቅ ማለት አንችልም።

የጦቢያ መፅሄት ዕዉቁ ብዕረኛና ዓምደኛ የነበሩት ሐሰን ዑመር አብደላ በባድመ ጦርነት ማግሥት „... ኢትዮጵያና ኤርትራ- ያልተጠናቀቀ ፍቺ፣ ያልተሳካ ጉርብትና...„ በሚል ርዕስ ፍራንክፈርት ጀርመን ይታተም በነበረ „ራዕይ„ በተሰኘ መፅሄት በኅዳር ወር 1991 ዓ/ም ዕትም መጣጥፋቸዉ „ ... አንድ መካድ የማይቻል ዕዉነታ አለ። ኢትዮጵያ፣ ኤርትራ የምትባል አዲስ ጎረቤት አገር አላት። ይህ ብዙዎቻችን ከራሳችን ጋር እንዲዋሃደን ያልተዘጋጀንበት ዕዉነታ ነዉ። ሊውጡት ያስቸገረ መራራ እንክብል። ለጊዜዉም ቢሆን ከዚህ ዕዉነታ ጋር ራሳችንን ማስታረቅ ካልቻልን ልክ እንደ ሻዕቢያ መሪዎች በሕልም ዓለም ተዘፍቀናል ማለት ነዉ።„ ይሉና በመቀጠልም „... በሁለቱ ሀገሮች መካከል ፍቺዉ አለመጠናቀቁ፣ ጉርብትናዉም ደግሞ አስቸጋሪ እየሆነ መምጣቱን በባድመ ሰበብ „የድንበር ጦርነቱ...„ ወለል አድርጎ አሳይቶናል።... ባንድ ጣራ ሥር ለመኖርም ሆነ፣ ጎን ለጎን በጉርብትና የኢትዮጵያን ሀገራዊ ጥቅም ማስከበር የሚቻለዉ የተፈጠሩትን ዕዉነታዎች ግንዛቤ በመዉሰድ ትክክለኛ እስትራቲጅካዊ ግቦችን በመንደፍ ነዉ„። በማለት ሀገራችንን ሊጎዳ በማይችል መልክ ሊሆን የሚገባዉን መፍትሄ ቁልጭ አድርገዉ አስቀምጠዋል። አሁን የተያዘዉ አካሄድ ግን ሻዕቢያን እሹሩሩ እያልን፣ ፕሬዚዴንት ኢሳይያስን እንደ ቀድሞዉ የስሜን ኮርያዉ ፕሪዚዴንት ኪምልሱንግ „ The Great and our beloved leadr...„ እያልን እያንቆለጳጰስን ብቻ ቶሎ ቶሎ ብለን ወያኔን ከሥልጣን እናስወግድ ነዉ። ፕሬዚዴንት ኢሳይያስን በተመለከተ ሰሞኑን ስለስደተኞች ጉዳይ ለመነጋገር የአፍሪካ እና የአዉሮፓ መሪዎች ማልታ ላይ የጋራ ጉባዔ ባካሄዱበት ወቅት አንድ የጀርመን ኮሜንታተር (ዘጋቢ) ጋዜጠኛ „...President Esaiyas gehort nicht auf die Africa-Europa conference sondern ins Gefangnis...„ (ፕሬዚዴንት ኢሳይያስ ወደ እሥር ቤት መጋዝ

የሚገባቸዉ እንጅ፣ የዚህ ጉባዔ ተሳታፊ መሆን የሚገባቸዉ ሰዉ አልነበሩም) ያለዉ አገላለፅ እርሳቸዉ የሚገኙበትን ሁኔታ በትክክል የሚገልፃቸዉ ይመስለኛል። ወያኔ ቢወገድ ብዙዎቻችን የምንፈነጥዝ እንጅ፣ አንገት የምንደፋ አይደለንም። ኢትዮጵያን በማጥፋት ደረጃ፣ ሻዕቢያና ወያኔ ሁለቱም በሠይጣንነት የሚፈረጁ እንጅ፣ አንዱ መላክ ሌላኛዉ ብቻ የሠይጣንነት ባሕርይ የሚለገሠዉ አይደለም። ቢቻል የሁላችንም ፀሎትና ትግል መሆን ያለበት ግብዓተ-መሬታቸዉ ባንድ ቀን እንዲፈፀም ነዉ። ዉልደተ-ቀናቸዉ ቢለያይም በባሕርያቸዉ በተለይም ኢትዮጵያን በማጥፋት መሠሪነታቸዉ መንትያዎች ናቸዉና።

ይህ ጉባዔ ከመካሄዱ በፊት በተለያዩ ድረ-ገፆች የነበረዉ እሰጥ-አገባ በኤርትራ በኩል የሚካሄደዉ የትጥቅ ትግል ያዋጣል አያዋጣም፣ በሚል ርዕስ ላይ ያተኮረ ነበር። ተመክሮ አለን በሚሉት በቀድሞ የኤርትራ ተመላላሾች በነደምስ በለጠና በሌላኛዉ ወገን የተላለፉትን መልዕክቶች ተከታትለናል። አሁንም በኤርትራ በኩል በሚደረግ ግንኙነት ነፃ መዉጣታችን ብዙዎቻችንን የማያሳምነን ዕዉነታ ቢሆንም፣ በጉዳዩ አምኖበት ግን ሕይወቱን የሚሰዋ ወገን ስላለ፣ ባናምንበትም ድርጊቱን በአደባባይ ለማዉገዝ ግን ሆዳችንን ያመናል። ደግሞም አንድ ድርጅት በሚያምንበት መንገድ መታገል መብቱ ነዉ። አባላቱንና እንደ ድርጅቱ የፖለቲካ ብስለት ሌላዉንም ሞብላይዝ አድርጎ ከጎኑ በማሰለፍ ዓላማዉን ዕዉን ሊያደርግ ይችላል። ጥያቄዉ ግን ከእስካሁኑ የሻዕቢያ አካሄድ በመነሳት ኢትዮጵያ እስካልፈራረሰች ድረስ ኤርትራ ሙሉ ነፃነቷን አግኝታ መኖር አይቻላትም የሚል ዕምነት እስካለዉ ድረስ እንዴት ከዚህ ዓይነቱ ድርጅት ጋር ሥጋዎ ደሙ (ሥርዓተ-ቁርባን) በመፈጸም ወይም በመቀበል ኢትዮጵያን ነፃ ማዉጣት ይቻላል ነው? አካሄዱ ሲፈተሽ ግን የኤርትራን ነፃነት ማደላደልና ለሁልጊዜም ዋስትና ለመስጠት እንጅ ተቃዋሚ ድርጅቶቻችን የኤርትራን ምድር ማኮብኮቢያ አድርገዉ ወያኔን በማስወገድ በትረ ሥልጣን ለመጨበጥ እንኳ ቢበቁ ለሻዕቢያ የሚያበረክቱት ገፀ-በረከት ምን ሊሆን እንደሚችል ገና በዉል የታወቀ ጉዳይም የለም። ሻዕቢያ ወያኔን ለምኒልክ ቤተ-መንግሥት እንዳበቃ ሁሉ፣ እኛንም ለዚያ ደረጃ እንዲያደርሰን ብለዉ ካመኑም፣ ኢሳይያስና ድርጅታቸዉ ሻዕቢያ ይህ ዓይነቱ መልካም ፈቃዳቸዉ እንኳ ሆኖ ቢገኝ፣ በአሁኑ ጊዜ የሻዕቢያ አቅም ሲፈተሽ፣ እራሱንም፣ አገሩንም እየገደለ ያለ ድርጅት ነዉ። በእርግጥ አርበኞች-ግንቦት 7 እኛ ለሥልጣን የምንታገል የፖለቲካ ድርጅት ባለመሆናችን፣ ብቻ ወያኔን እናስወግድ እንጅ፣ ከዚያ ባሻገር ያለዉ ተግባር እንደማይመለከታቸዉ ሲያስገነዝቡ የሚደመጥ ከሆነ፣ ከዚች ጎረቤት አገር ጋር ምን ያህል ቢያሳስባቸዉ ነዉ፣ በእጅ አዙርም ቢሆን መድረኮች እየተዘጋጁ ስብከቶች የተጀመሩት? የሚል ጥያቄ መነሳቱ የማይቀር ይሆናል። ወያኔ ለሻዕቢያ ባለዉለታነቱ ኤርትራን እራሷን ከሁለት ወደቦች ጋር አስረክቧል። እስከ ባድመ ጦርነት ወቅትም ኢትዮጵያን በበላይነት እንዲያስተዳድሩና እንዲመሩ ፈቅዷል። ሐብቷንም እንዲዘርፉ አድርጓል። ከኢትዮጵያ ቡና ወደ ኤርትራ እየተጓዘ ኤርትራ በዓለም በቡና አምራችነት 14ኛ ደረጃ ምድብ ደርሳ እንደነበር ተረሳ። እረ ስንቱ? የወርቅ ጥርሳቸዉ ሳይቀር እየተነቀለ ከኤርትራ ምድር በግፍ የተባረሩት ወገኖች ሰቆቃ አራሙቻ ይጫንበት? እነ በዛብሕ ጴጥሮስ ተረሱ? ኢትዮጵያን የማፈራረሱ የመቶ ዓመቱ የኢሳይያስ የፖለቲካ ቀመር ተዘንግቶና በትናንቱ የባድመ የድንበር ጥያቄ ሰበብ ትርጉም አልባዉ ጦርነት የተቀጠፈዉ የሰዉ ሕይወት ደም እየጮኸ፣ እሱን ነፃ አዉጭ ነቢያችን አድርገን እንቀበለዉ? ወገኖቼ በሽተኛ መሆን ነዉ ትርፉ። አቅም የሌለዉ እንዳዉ ዝም፣ ግን አያስችል። አገርን ረስቶ እንዴት መኖር? እንዴትስ ዕንቅልፍ ሊወስድ ይችላል?

የተነሳሁበት ነጥብ የሰሞኑን የዋሽንግተኑን ስብሰባ አስመልክቶ በተንፀባረቁት ጉዳዮች ላይ አቀራረቡ ኢትዮጵያን የሚጎዳ መስሎ ስለታዬኝ፣ያለፈዉን ለመተቸት ብቻ ሳይሆን፣ ቢያንስ ቪዥን ኢትዮጵያ በሚቀጥለዉ ዓመት ማርች 25 እና 26/2016 ሊያካሂድ ባቀደዉ ጉባዔው ተመሳሳይ ስሕተቶች እንዳይፈጸሙ ለማስገንዘብም ጭምር ነዉ። በጉርብትና መኖር ያለባቸዉ የሁለቱ ሀገሮች

መቀራረብ አስፈላጊ ብቻም ሳይሆን ግዴታም ነዉ። ግን እንዴትና በምን መልኩ? ለዚህ ጥያቄ መሠረታዊ መልሥ ከሚሰጠዉ ,,... ኢትዮጵያና ኤርትራ-ያልተጠናቀቀ ፍቺ ያልተሳካ ጉርብትና...,, ከሚለዉ የሐሰን ዑመር አብደላ መጣጥፍ በተጨማሪ የካናዳዉ ኗሪ የሆኑት ተክለሚካኤል አበበም ,,...የኤርትራ ነገር፤ የኛ ችግር፤ መርህ አልባ ፍቅር...,, በተሰኘ ርዕስ የሁለቱን አዲስ ተጎራባች አገሮች የወደፊት ግንኙነት አስመልክቶ፤ ሁላችንም የምናምንበትን መንገድ በተባ ብዕራቸዉ ቁልጭ አድርገዉ አስቀምጠዉታል። ወደፊት ሊተኮርበትና ሊሆን የሚገባዉም ይላሉ ተክለሚካኤል ,,... ስለሁለቱ ሀገሮች ብሄራዊ ጥቅምና ሁለቱ አገሮች አንዳቸዉ ያንዳቸዉ ሥጋት ሳይሆኑ፣ ስለሚኖሩበት ሁኔታ፣ በሁለቱ ሀገሮች መካከል ለሚኖር ሰላማዊ ግንኙነት እንቅፋት ስለሚሆኑ ነገሮች፣ ወደፊትም ስለሚያጋጥሙ ተግዳሮቶች...,, መሆን ይኖርበታል። በዚህ ጉባዔ ከተደመጡት ቁምነገሮችና ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ወገን ያስደሰተዉ አቀራረብ ቢኖር፣ የፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም አሜሪካ በኢትዮጵያ ላይ ስለምታራምደዉ የደባ ፖሊሲ በማስረጃነት እያስረገጡ በሁለቱም የሀገሪቱ አምባሰዶሮች ፊት ያስተላለፉት ምሉዕ-በኩለሄ የሆነዉ መልዕክት ነበር።

ባጣቃላይና ባጭሩ የኢትዮ-ኤርትራን ዘላቂ ግንኙንነት አስመልክቶ ምን መደረግ አለበት? የመጀመሪያው ተግባር እኛ ኢትዮጵያዉያን በቃ ባይዋጠንም የኤርትራን ነፃ አገር መሆን እንቀበል። በታሪክ ወደኋላ ተጉዘን ተጠያቂዉ አፄ ምኒልክ ናቸዉ፣ ወይም አፄ ኀይለሥላሴ ወይም ደርግ ነዉ እያልን ከምንነታረክ ያን ፋይል ዘግተን ወደፊት እንዴት በሰላማዊ መንገድ በጉርብትና መኖር እንደምንችል እንምከር፣ እንዘክር። እነሱ በጊዜያቸዉ የሚያምኑበትን ሠርተዉ አልፈዋል። ሠላም እንስጣቸዉ። ብናወግዝና ብንራገም የሞቱትን፣ ብንፎክርና ብናቅራራ በሕይወት የሌሉትን ሥም እያነሳን። መቼ ነዉ ያሁኑ ትዉልድ የራሱን ታሪክ ሠርቶ የሚያልፈዉ? በእርግጥ ታሪኩን እንወቀዉ። ለልጆቻችንም ደግ ደጉን እናውርሳቸዉ። ቴዲ ,,... እስኪ እንሞክረዉ ደግሞ ተለያይተን...,, እንዳለዉ ተለያይቶ መኖሩ እየተሞከረ ስለሆነ፣ ካልተቻለ ደግሞ እኛ ላናየዉ ብንችልም እንደገና አብሮነቱ ከራሱ ከሕዝቡ ጥያቄዉ ይመጣል። ይህ የጊዜ ጥያቄ እንጅ አይቀሬ ነዉ። ያንጊዜ ነዉ የማዳግም መፍትሄ የሚገኘዉም። እስከዚያዉ ድረስ ግን የሁለቱን አገሮች፤ የትናንት፣ የዛሬንና የነገን ግንኙነት አስመልክቶ፣ ጉባዔዎች ሲደረጉ፣ ዉይይቶች ሲካሄዱ፣ አንደኛዉ የሌላኛዉን አገር ጥቅም በሚጎዳ መልኩና ከሐቅ የራቁ ጉዳዮችን በማስተናገድ የመርሕ አልባ ጭፈራዎች ሲደረጉና ከበሮዎች ሲመቱ በሀገሬ ጉዳይ ያገባኛል ባዩ ሁሉ እራሱን ይታመማል። እንደ ሰሞኑ የካሳ ክበደ ምሥክርነት ማለት ነዉ። ስለዚህ ኤርትራን ተዋጠልንም፣ አልተዋጠልንም እንደ ሌሎቹ ጎረቤት አገሮች፤ እንደነ ሱዳን፣ እንደነ ኬንያ፣ እንደነ ጅቡቲ እንቁጠራት። ከዚያም አንዱ አንዱን አሸንፎ ሥልጣን ለመያዝ በሚደረግ የእሽቅድድም ሩጫ ሳይሆን ግንኙነቱ በመርኅ ላይ በተመሠረተ እና የሁለቱንም አገሮች ብሔራዊ ጥቅም ባስጠበቀ መልኩ በሚጣል የማዕዘን ድንጋይ ላይ መሆን ይኖርበታል። እንዲያዉም ከኤርትራ ጋር የሚኖረን ግንኙነት ከሌሎች አጎራባች አገሮች በተለየ መልኩ መታየትም ያለበት ነዉ። የቅኝ ገዥነትና ተገዥነት ታሪኩን አምነን ለመቀበል ለብዙዎቻችን መራር ፅዋ ቢሆንብንም፣ ኢትዮጵያን እንደነሱ እምነት ቅኝ ገዥ አገር አድርገን በንወስድ እንደ ሌሎች ቅኝ ገዢ አገሮች የጂኦግራፊ ርቀት ባለመኖሩ በኩታ-ገጠምነት በሚኖረን የጧት ማታ ግንኙነት ላይ የተለየ ተፅዕኖ ማሳደሩ ግድ ነዉ።

ሞዛምቢክ፣ አንጎላ፣ ወይም ብራዚል ከፖርቱጋል ጋር፣ ወይም ፈረንሳይ ከጁቡቲ ጋር፣ የእኛ ዓይነት ችግር የለባቸዉም። በጂኦግራፊ (በመልከዓ ምድር) አቀማመጥ የተሳሰሩ አይደሉምና። ርቀታቸዉ የት እየለሌ ነዉ። በመሆኑም የግድ የኤርትራና የኢትዮጵያ የሁለቱ አገሮች ጎን ለጎን በሰላማዊ የጉርብትና ወግና ልማድ የተሳሰረ፣ በፖለቲካ መርሕ ቀመር ላይ በተመሠረተ የጉርብትና ፍልስፍና ጎን ለጎን መኖር መቻል ግድ ይላል። አዲስ አስተሳሰብ ይፈጠር። የሦሥት አራት አሰርት ዓመታት በደም የዋጀ የጦርነት ታሪካችን እንዲረሳ፤ የቂም በቀል ነቀርሳ ከኅሊናችን እንዲነቀል የሰላም

መዝሙር በመካከላችን ይዘመር። ሻዕቢያም፣ ወያኔም ተወግደዉ ለሁለቱ አገሮች ጤናማ ግንኙነት ራዕይ የሚኖራቸዉ መንግሥታት የሚፈጠሩበት የፖለቲካ ፍልስፍና የሚሰበክበት አካሄድ ይቀየስ። የማስመሰል አካሄድ ይቁም። በሀገር ብሔራዊ ጥቅም ሽፍጥ የተሞላበት ካባ ደርበን ለሥልጣን እንኳ መብቃት ቢቻል መጨረሻዉ ሁሉ የዕንቧይ ካብ ነዉ የሚሆነዉ። ትናንት የተሰራን ስሕተት ዛሬ መድገም ሳይሆን፣ መማር ያለብን ከትናንቱ ስሕተታችን ነዉ። ትናንት ብቻ ደርግ ይዉደቅ እንጅ፣ የፈለገዉ ይምጣ የሚል መፈክር አንግበን ስንጮህ፣ ከወርቁ ብሄረሰብ የተፈጠረና ባንዲራችንን በጨርቅነት ለፈረጀ መሪና መንግሥት ተዳረግን። ሌላዉንም እየሆነ ያለዉን ይኸዉ፣ ከሃያ አምስት ዓመት ላላነሰ ጊዜ እያየን ስለሆነ፣ የአሁኑም ሩጫ ከዚያ ቢብስ እንጅ ለብሩህ ተስፋነት የሚያስተነብይ አይደለም።

አሁን የሚታየዉ አካሄድ የትም አያደርስም። ጉባዔዉን ደከመዉ ማዘጋጀታቸዉ ይደነቃሉ። ግን አቅጣጫዉን እየሳተ ስለሆነ ድካማቸዉን ሁሉ ከንቱ ያስቀረዋል። ምንም እንኳን ወያኔን ብንጠላም የፕሬዚዴንት ኢሳይያስና የሻዕቢያ ዕድሜ ለማኞች መሆን ግን አይገባንም። እንዲያዉም አንድ ኤርትራዊ የሻዕቢያ ኤርትራ ተቃዋሚ ግለሰብ ይህን ጉባዔ „..የኢትዮጵያ መንግሥት ተቃዋሚዎች ከፕሬዚዴንት ኢሳይያስ ደጋፊዎች ጋር ያካሄዱት የጋራ ጉባዔ ነበር...„ የሚለዉ አሽሙር አዘል አባባል ጉባኤዉን በትክክል ይገልጸዋል ቢባል ተጋነነ ሊባል አይገባዉም። በትክክል የተንጸባረቀዉም ይኸዉ ዕዉነታ ነበር። ስለአቶ ኢሳይያስ ለኢትዮጵያ በጎና ቅን አሳቢነት መድረክ አዘጋጅቶ በነካሳ ከበደ ካድሬነት መሰበክ የለበትም። ልጅ ካሳ ከበደ ለፕሬዚዴንት ኢሳይያስ ሽንጣቸዉን ገትረው ምስክርነት መስጠታቸዉ እምነታቸዉ ከሆነ ባልከፋ፣ ግን እንደዚህ በአደባባይ ሰዉ ፊት ቆመዉ ለሌላ ሰዉ የመመስከር የታማኝነት ሰብዕና እራሳቸዉ አላቸዉ ወይ ነዉ ጥያቄዉ? እንደ ነአምን ዘለቀ ወጣት ፖለቲከኛ ለሆነ ሰዉ ደግሞ ምን እንደነካቸዉ እንጃ እንጅ፣ የጂድ ካሳ ከበደ የነፍስ አባትነትና የጡት ልጅነት ለመሆን የሚዳዳቸዉ ሰዎች መሆን አልነበረባቸዉም። ከእሳቸዉ ጋር መጠጋትና መሞዳሞድም እንደማያስፈልግ፣ በተባበሩት መንግሥታት መድረክ ለሃገራቸዉ ሽንጣቸዉን ገትረዉ ሲከራከሩ የነበሩትን አምባሰደር ብርሃኑ ዲንቃን በሕይወት እያሉ ጠይቀዋቸዉ ቢሆን ኖሮ፣ ባጠገባቸዉ አያልፉም ነበር። እንዲያው ለመሆኑ ይህን ስለኢሳይያስ ምስክርነት ሲናገሩ የቀድሞ አለቃቸዉ ፕሬዚዴንት መንግሥቱ ኃይለማርያም ምን ሊሰማቸዉ እንደሚችል አጠገባቸዉ ሆኖ ለአንድ ደቂቃ የማስተዋል ዕድሉ ለገጠመዉ ሰዉ ምንኛ መታደል ነበር። በእርግጠኝነት ግን „.. ነይማ ውባንች በፈጠረሽ ይህን አክሮባት ሥሪ ስሚዉ (ተመልከችዉ) ...„ ማለታቸዉ እንደማይቀር መቶ በመቶ እርግጠኛ ሆኖ መናገር የሚቻል ይመስለኛል። ቀጠል አድርገዉም፣ ለነገሩ በእሱ መፍረድ አልችልም። እኔም አሥራ ሰባት ዓመት ሙሉ በቴዎድሮስ ስምልና ስገዘት ኖሬ ነዉ፣ አሥራ አንደኛዉ ሰዓት ሲደርስ ብርክ ይዞኝ፣ የመቅደላን ጉዞ ትቼ ወደ ሐራሬ ያመራሁት። ካድሬዎቼ ከእኔ የሚሻሉ ይመስሉኝ ነበር እንጅ፣ የቃል-አባይነቱ ቁንጮማ እኔዉ እራሴ መሆኔን አልስተዉም። አያይዘዉም የፈለገ ይሁን እንጅ ግን ኢሳይያስን አስመልክቶ እንዲህ ዓይነት ወደል ዉሸት አይዳዳኝም ብለዉም ይጨምሩበታል። መተማመን እንድንችል ግን እስኪ ዕድሉ ያላችሁ ነፃ ፕሬሶች እባካችሁ በእግዚአብሄር በዚህ ጉዳይ ዙሪያ አነጋግሯቸዉና የሚሉትን እንስማ። ለናንተም ለኤርምያስ ለገሠ የቴሌቪዝን መስኮታችሁ ፊት መቀየሪያ ይሆናችሁኣል። ፕሬዚዴንት ኢሳይያስ በማናቸዉም ዓይነት የፖለቲካ ሚዛን ለኢትዮጵያ ነፃ መዉጣት እሥራኤላዊዉ ሙሴ ሊሆኑን አይገባም። ሳውል ጳውሎስን መሆን ይቻል አንጅ፣ ኢሳይያስ ግን በምንም ተዓምር ጳዉሎስን ሊሆኑ አይችሉም። ጉባዔዎች በሽፍጥ አይሞሉ። የሸር ገመድ አይፍተልባቸዉ። እረ እየተስተዋለ ወገን!